# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*
(አንድነት/United)

የካቲት ፳፯ ቀን ፪ ሺህ ፱ ዓ. ም
March 6, 2017

# አሁንም ዓድዋ

የካቲት 23ን ስናነሳ ሕዝባችንንና ሃገራችንን በሚመለከት ብዙ ጉዳዮችን በአእምሯችን እንድናጉላላ ይቀሰቅሰናል። በርካታ ጥሩና መጥፎ ስሜቶችንም ከታመቁበት አውጥቶ እንድናስብበት ያደርገናል።

ዓድዋ በዋናነቱ አያት ቅድመ አያቶቻችን አገራችንን ሊያራክስ፣ ሕዝባችንን ባሪያው አድርጎ ሊገዛ ከሩቅ ተነስቶ፣ ባሕር አቋርጦ የመጣን ወሽካላ ጥሊያንን አንገቱን በጎራዴ ቀልተው፣ መድፉን በመድፍ ፈነካክተው፣ አይቀጡ ቅጣት ቀጥተው፣ የተጠቃ ውሻ ይመስል ጅራቱን በእግሩ መሃል ወሽቆ፣ በሃፍረት አንገቱን ደፍቶ ወደመጣበት እንዲመለስ ያደረጉበትና ታሪካዊ ድል የተቀዳጁበት ነው። ከዚያም አልፎ ግን ይኸው እስከ አሁን ድረስ፣ እኛነታችንን በማላበስ፣ ደረታችንን ነፍተን በኩራት ኢትዮጵያዊ ነን ብለን እንድንፎክር ያስቻለ ግኝት ነው።

ታሪክ ነውና የምንኮራበትን ማንነታችንን ሳንዘነጋ፣ በዚያው ወቅት በኒያ እፁብ ድንቅ በሚባሉ ጀግኖች መሃል የተፈጠሩ አንዳንድ ጉዶች፣ ለጠላት አድረው ከጠላት ጎን ተሰልፈው ወገናቸውን እንዳጠቁ ሳንረሳ ውዳቂ በመሆናቸው ከኢምንት ሳንቆጥራቸው፣ ዳግም እንዳይደገም ለትምህርታዊነቱ ሲባል በታሪክ ዘግበን እናልፈዋለን።

ዓድዋን ስናነሳ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በበርካታ ብሄሮችና ብሄርሰቦች የተሞላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ፣ የጣሊያን ግዛት ከነበረው ኤርትራ አንስተው፣ የጎንደርን፣ የጎጃምን፣ የትግራይን፣ የወሎን፣ የሸዋን፣ የአርሲን፣ የወለጋን፣ የከፋን፣ የሐረርን፣ የሲዳሞን፣ የባሌን፣ የጋሞጎፋን ሕዝብ ሁሉ ቀስቅሰው፣ ክተት ብለው እንደ አንድ ችቦ ጠምረው እንደ አንድ ሰው ለጦር ያዘጋጁበት ጊዜ ነው። ይህ የሀገር ፍቅር፣ ይህ አንድነት ነው ያለ ዘመናዊ ቋሚ ወታደራዊ መዋቅር፣ ባልተሟላ ትጥቅና ስንቅ፣ ያለ ምንም ዓይነት ወታደራዊ

**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **eprp_united@eprp-ihapa.com**

ትምህርትና ዝግጅት፣ በቀበሌና በጎበዝ አለቃ እየተመራ፣ በጎራዴና በጦር ብቻ በርካታ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ታጥቆ፣ በዘመናዊ ቋሚ የጦር አደረጃጀት ተደራጅቶ በቂ ትጥቅና ስንቅ ሰንቆ የመጣን ጠላት በአንድ ፀሐይ አጥቢያ ድባቅ መትቶ ሽንፈትን ያከናነበው። ከዚህ አንድነት ጋር ዓድዋን ስንዘክር ሁሌ ከፊታችን ድቅን የሚሉትን አኩሪ ድል እንዲቀዳጅ ያደረጉት ቆራጥ ወታደራዊ አመራር የሰጡት እቴጌ ጣይቱ ብጡልን፣ የትግራዩን ራስ መንገሻ ዮሐንስ፣ ራስ አሉላ አባነጋንና ራስ ስብሃትን፣ የሸዋውን ባልቻ አባነፍሶንና፣ ፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስን፣ የሐረሩን ራስ መኮንንን፣ ኤርትራዊው ደጃዝማች ባህታና የውስጥ አርበኛ በመሆን ለጄነራል ባራቲዬሪ ያልሆነ መረጃ በመስጠት በኢትዮጵያውያኑ ወጥመድ እንዲገባ በማድረግ ትልቅ ሚና የተጫወቱት አውዓሎም፣ የጎንደሩ ራስ ወሌ ብጡል፣ የላስታው ዋግሹም ጓንጉል፣ የኦሮሞው ባላባት ራስ ጎበናና እንዲሁም፤ ራስ ሙሉጌታ ይገዙ አማኢትና ሌሎች አይበገሬ፣ ቆራጥና ፍንክች የማይሉ አርበኛ መሪዎቻችንን እናስታውሳለን።

ይህ አንድነት፣ ይህ ወኔ፣ ይህ ጀግንነት የኢትዮጵያ አገራችንን ነፃነት አስከብሮ፣ አፍሪካን እንደ ቅርጫ ሊቀራመት በበርሊን ጉባዔ ወስኖ የነበረን የነጭ መንጋ ጥጉን እንዲይዝ አድርጎ፣ አሁን ድረስ ከአፍሪካ በቅኝ ያልተገዛች ብቸኛ አገር መሆኗን አስረግጧል። ለአፍሪካውያን ጥቁሮች ብቻ ሳይሆን ከአፍሪካ ውጭ ተበታትነው በአውሮፓና አሜሪካ በባርነት ሥርዓት ሥር ሞራላቸው ተንኮታክቶ ለነበሩት ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ተስፋ በመስጠት የኩራት ካባ አከናናቢም ሆኗል።

ከሁሉም በላይ ግን የዓድዋ ዋና ውጤት ከቴዲ አፍሮ ዘፈን የተወሰደው "ወይ ባልለው ያኔ፤ እኔን አልሆንም ነበር እኔ" የሚለው ስንኝ በሚገባ ይገልጸዋል። በአፄ ምኒልክ አስተባባሪነትና መሪነት አንድ ሆኖ ድል የተቀዳጀው ሕዝባችን ውስጥ የፈጠረው እኔነት፣ አንድነትና ኢትዮጵያዊነት በዋናነት የሚጠቀስ ነው። ይህ እኔነት/አንድነት ከዓድዋም አልፎ ጥሊያን እንደገና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት፤ ካለፈው ጊዜ በበለጠ ዝግጅትና አዳዲስ የጦር መሣሪያዎች ታጥቆ መልሶ ቅኝ ሊያደርገን ሲመጣ፣ ያ የዓድዋ የአንድነት መንፈሱ ያልረገበው ሕዝባችን አሁንም በቆራጥነት አምስት ዓመት ሙሉ በአልቤንና በወጨፎ ብቻ በታንክና በአይውሮፕላን የታጀበን ወራሪ ኃይል መቀመጫ በመንሳት አቸንፎ የሃገሩን ነፃነትና ድንበር ማስከበር ችሏል።

ጣሊያን ቢያሸንፍ ኖሮ፣ የእኔነት፣ የአንድነትና የአልበገር ባይነት ወኔ አያብብም ነበር። በኢትዮጵያውያን ውስጥ የሚንፀባረቀው ራስን የማክበርና ከፍ አድርጎ ማየት ቀርቶ በሌሎች በቅኝ ተገዥነት ያለፉ ሕዝቦች ውስጥ የሚታየው የበታችነት ስሜት ሊያድግ ይችል ነበር። በአጭሩ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ግንባር ላይ የሚነበበውን ኩራት ያላበሰንና የኢትዮጵያዊነትን እኔነት እንዲያብብ ነው ዓድዋ ያደረገው።

ይህ የዓድዋ መንፈስ፣ ይህ የዓድዋ አንድነት፣ ይህ የዓድዋ አይብገሬነት አሁንም እንዳለ ነው። ይህ የእኔነት/ኢትዮጵያዊነት መንፈስ ነው አሁንም አገር በቀል የሆኑ ከሃዲዎችና ባንዳዎችን እንድንታገላቸው ያስቻለን። ይህ የዓድዋ እኔነት ባይኖር ኖሮ አገራችንንና ሕዝባችንን በዘርና በቀየ ለመሸንሸን ሌትተቀን ያልቦዘኑት ጠባብ ብሄረተኞችና አድሃሪዎች እቅዳቸው ግብ ይመታ ነበር። አሁንም የሀገራችንን የግዛት አንድነትና የሕዝቧን ሉዓላዊነት ሊያስከበር የቻለው ይህን የዓድዋን መንፈስ ነው ሎሬት ጸጋዬ ገብረመድኅን

“ዋ!
ዓድዋ የዘር ዓፅመ ርስትዋ
የደም ትቢያ መቀነትዋ
በሞት ከባርነት ሥርየት
በደም ለነፃነት ስለት
አበው የተሰዉብሽ ለት፤
ዓድዋ
<u>የኩሩ ትውልድ ቅርስዋ</u>
<u>የኢትዮጵያነት ምስክርዋ</u>
ዓድዋ”[1]

ብሎ የተቀኘለት።

ያኔ በባንዳነት ጣሊያንን እየመሩ አርበኞች አያቶቻችን የተዋጉት የልጅ ልጆች ዛሬም ጣሊያን ዳግም ወደ አገራችን በተመለሰ ጊዜ ኢትዮጵያውያንን በዘር ከፋፍሎ ለማዳከም ያወጣውን የዘረኝነት ክልል ያለምንም ማዛባት በትክክል ከሥራ ላይ ለማዋል ኅሣን

---

P.O.Box 91384 Phone: 202- 241 2078
Los Angeles, CA 90009 eprp_united@eprp-ihapa.com

መሠረት ያደረግ ፌደራሊዝም ቀርጸው አገራችን እያወኩ ይገኛሉ። ይህን ከውጭ ወራሪ ያልተናነስ የህወሓትን አገዛዝ እንደ ዓድዋው ሁሉ ዛሬም በአንድነት ተነስተን አሽቀንጥረን ጥለን ለሁላችንም የምትበጀውን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መገንባት የግድ ይላል። ሁልጊዜ ዓድዋን እየዘከርን መኖር ብቻ ሳይሆን ከዓድዋ የተማርነውን የአንድነት፤ የአብሮነት፤ የይቅርታ ትምህርት አዲሱ ትውልድ ሊማር ይገባዋል። ተቃዋሚ ኃይሎች ልዩነታቸውን አጥብበው፤ የተቀያየሙ ለኢትዮጵያ ሲሉ ይቅር ተባብለው አገራችን ሊያድኗት ይገባል።

የዓድዋ የእኔነት መንፈስ ይለምልም!

**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **eprp_united@eprp-ihapa.com**